በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ.መ.ቁ 233903
ጥቅም 08 ቀን 2015 ዓ.ም

ዳኞች:- እትመት አሠፋ
ተሾመ ሽፈራው
ኑረዲን ከድር
መላኩ ካሣዬ
እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1. አቶ ዳዊት አባይነህ --- ባለቤታቸው ነኝ ያሉ ወ/ሮ ቬኑስ አባይነህ ቀረቡ
2. አቶ ናትናኤል ሽፈራው - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- የኦሮሚያ ዓቃቤሕግ - አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች ነሐሴ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የምዕራብ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 61944 ሐምሌ 25 ቀን 2014 ዓ.ም የአመልካቾችን የዋስትና መብት በመንፈግ የሰጠው ብይን፣ ይህን ብይን በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 401575 ነሐሴ 13 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 406112 ነሐሴ 20 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካቾች ላይ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምዕራብ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካቾች የአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 168/2 ድንጋጌን በመተላለፍ ሹፌር ሆነው ብር 263720 / ሁለት መቶ ስልሳ ሶስት ሺህ ሰባት መቶ ሀያ / የሚገመት ዕቃ የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-78618 ኦ.ሮ በሆነ ተሽከራካሪ ጭነው የኮንትሮባንድ ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡

አመልካቾች በጠበቃቸው አማካኝነት የዋስትና መብታቸው እንዲፈቀድላቸው ጠይቀው ዓቃቤሕግ በሰጠው አስተያየት አመልካቾች የተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ ዋስትናን ባያስከለክልም አመልካቾች ሹፌሮች ስለሆኑ ከቦታ ቦታ እየተንቀሳቀሱ የሚኖሩ ስለሆነ እና አድራሻቸውም ሌላ ቦታ ስለሆነ፣ በዚህ ዓይነት ወንጀል የሚከሰሱ ሰዎችም ዋስትና በማስያዝ ተመልሰው የማይቀርቡ ስለሆነ የአመልካቾች የዋስትና መብት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት ሊከለከል ይገባል በማለት ተቃውሟል፡፡

ፍርድ ቤቱም በግራቀኙ የቀረበለትን የዋስትና ክርክር መርምሮ አመልካቾች የተከሰሱት በኮንትሮባንድ ወንጀል ነው፣ የመኖሪያ አድራሻቸውም ሌላ ቦታ ነው፣ የስራ ሁኔታቸውም ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚያንቀሳቅሳቸው በመሆኑ የተከሰሱበት ወንጀል የዋስትና መብትን የሚያስከለክል ባይሆንም በዋስ ቢወጡ ተመልሰው ሊቀርቡ እንደሚችሉ አያሳምንም በማለት አመልካቾች ያቀረቡትን የዋስትና መብት ጥያቄ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት ውድቅ አድርጎታል፡፡

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

አመልካቾች ነሐሴ ቀን 2014 ዓ.ጀም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- አመልካቾች ቋሚ አድራሻ ያለን መሆኑ እየታወቀ ሾፌር በመሆናችን የዋስትና ግዴታቸውን አይወጡም በሚል ምክንያት የዋስትና መብታችን በመከልከል የተሰጠው ውሳኔ ማንኛውም ሰው ተንቀሳቅሶ የመስራት እና የመዘዋወር መብቱን በመጣስ የተሰጠ በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ የዋስትና መብታችን ሊከበርልን ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪው ችሎት ተመርምሮ አመልካቾች አሽከርካሪ በመሆናቸው ብቻ ቋሚ አድራሻ እንደሌላቸው በመግለጽ እንዲሁም በዋስትና ከተለቀቁ ወደ ፍርድ ቤት ላይመለሱ ይችላሉ በሚል ጠቅላላ ምክንያት በመጥቀስ አመልካቾች ያቀረቡትን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ ዋስትና ሊከለከል የሚችልበትን ሁኔታ አስመልክቶ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 ድንጋጌ ላይ ከተመለከተው አንጻር ለመመመርመር የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ መስከረም 05 ቀን 2015 ዓ.ም በሰጠው መልስ አመልካቾች ቋሚ አድራሻ ያላቸው መሆኑን ስለማስረዳታቸው መዝገቡ አያመለክትም፤ አመልካቾች ወደ ተለያዩ ስፍራዎች እየተዘዋወሩ የሚሰሩ ስለሆነ የዋስትና ግዴታቸውን አክብረው ፍርድ ቤት ሊቀርቡ አይችሉም፤ አመልካቾች የቀረበባቸውን ክስ እንዲከላከሉ ብይን ተሰጥቷል፤ መከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ እድል ተሰጥቷቸው ሳያቀርቡ ቀርተው ለ4ኛ ጊዜ ተቀጥሯል፤ ስለሆነም በዋስ ወጥተው ለመጥፋት እንዳለሙ የሚያሳይ በመሆኑ የዋስትና መብታቸው በመከልከል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ብይን ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ እንደቻልነው አመልካቾች የተሰሰሱበት የአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 168/2 ድንጋጌን ዋስትናን የማያስከለክል ሲሆን የስር ፍርድ ቤት አመልካቾች የዋስትና መብታቸውን አስመልክቶ ያቀረቡትን ጥያቄ ውድቅ ያደረጉት የአመልካቾች አድራሻ ሌላ ክልል ነው በኮንትሮባን ወንጀል ተጠርጥረው በዋስ የሚወጡ ሰዎች በተጨባጭ እየቀረቡ አይደለም በሚል መሆኑን ነው፡፡ በመሠረቱ የተያዙ ሰዎች በሕገ-መንግስቱ ጥበቃ ከተደረጉላቸው መብቶች አንዱ የዋስትና መብት ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 19/6 የተያዙ ሰዎች በዋስትና የመፈታት መብት ያላቸው መሆኑን በመርህ ደረጃ ያስቀመጠ ሲሆን ይህ በሕገ መንግሥቱ የተከበረው መሠረታዊ መብት ሊነፈግ፣ ሊገደብ ወይም በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ የሚደረገውም አግባብነት ባላቸው ሌሎች ዝርዝር ሕጎች መሠረት በልዩ ሁኔታ ነው፡፡

ይህን መሠረታዊ መብት አስመልክቶ የመወሰን ስልጣን እና ሃለፊነት የተሰጣቸው ፍ/ቤቶችም በወንጀል ጉዳይ ተጠርጥሮ ክስ የቀረበበት ሰው የሚያቀርበውን የዋስትና መብት ጥያቄ እና ከሣሽ የሆነው ዓቃቤሕግም በጉዳዩ ላይ የሚሰጠውን አስተያየት በሕገመንግስቱ ዋስትናን አስመልክቶ ከተደነገገው ድንጋጌ መሠረታዊ ዓላማ እና በሌሎች ልዩ ሕጎች ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በጥንቃቄ መርምረው ውሳኔ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህንኑ ተግባራዊ ሲያደርጉም በመርህ ደረጃ የዋስትናን መብት መፍቀድ ያለባቸው ሲሆን በሕጉ ተለይተው በተቀመጡ ምክንያቶች ግን የዋስትናን መብት በልዩ ሁኔታ ሊነፍጉ ይችላሉ፡፡

የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ሕግ ቁጥር 67/ሀ/ ዋስትና ከሚከለከልባቸው ልዩ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ የዋስትና ግዴታውን በማክበር በቀነ ቀጠሮው ሊቀርብ የማይችል መሆኑን ፍርድ ቤቱ ካመነ፣ የዋስትና ጥያቄውን ውድቅ ማድረግ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ሆኖም ይህን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ፍ/ቤቶች የተከሳሽን የዋስትና መብት መከልከል የሚችሉት በዘፈቀደ ሳይሆን ተከሳሹ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ ሊቀርብ አይችልም የሚያስብሉ በቂ እና አሳማኝ ምክንያቶች በተገኙ ጊዜ ስለመሆኑ ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካቾች የተከሰሱበት የሕግ ድንጋጌ በዋስ የመለቀቅ መብትን የሚከለክል አይደለም፡፡ የስር ፍ/ቤት የአመልካቾችን በዋስ የመለቀቅ መብት ውድቅ ያደረጉት  የተከሰሱት በኮንትሮባንድ ወንጀል ነው፤ የመኖሪያ አድራሻቸውም ሌላ ቦታ ነው፤ የስራ ሁኔታቸውም ከአንድ ቦታ

ወደ ሌላ ቦታ የሚያንቀሳቅሳቸው በመሆኑ የተከሰሱበት ወንጀል የዋስትና መብትን የሚያስከለክል ባይሆንም በዋስ ቢወጡ ተመልሰው ሊቀርቡ እንደሚችሉ አያሳምንም በሚል ነው፡፡
የስር ፍርድ ቤት የአመልካቾችን የዋስትና መብት በዚህ አግባብ ውድቅ ያደረገ ቢሆንም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 32 ለማንኛውም ኢትዮጲያዊ ከተረጋገጠው የመዘዋወር መብት አኳያ አመልካቾች በሐገሪቱ አካባቢ የመዘዋወር እና የመኖሪያ ቦታ የመመስረት መብት አላቸው ፡፡ ስለሆነም  አመልካቾች የሌላ ቦታ ነዋሪ መሆናቸው ብቻውን በሕገ መንግስቱ  አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ 6 የተረጋገጠላቸው በዋስ የመልቀቅ መብት እንዲነፈግ የማድረግ እና  በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 25 የተደነገገውን በሕግ ፊት እኩል የመሆንና እኩል የሕግ ጥበቃ የማግኘት መብትን የሚጥስ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው ምክንያት አይደለም፡፡ በሌላ በኩል የስር ፍርድ ቤቱ በኮንትሮባንድ ወንጀል የተከሰሱ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ አመልካቾች በዋስ ቢወጡ ሊቀርቡ አይችሉም የሚል ግምት የያዘ ቢሆንም ወንጀል ግላዊ ከመሆኑ አንጻር በኮንትሮባንድ ወንጀል የተከሰሰ ሰው ሁሉ ፍርድ ቤት አይቀርብም በሚል ድምዳሜ የሚወሰድበት አይደለም፡፡ በዚህ ረገድም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎ በሰ.መ.ቁ 225533 ሠኔ 28 ቀን 2014 ዓ.ም አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡
ስለሆነም በየደረጃው ያሉ የክልሉ ፍርድ ቤቶች የአመልካቾች አድራሻ ሌላ ክልል ነው፤ በኮንትሮባንድ ወንጀል የተከሰሱ ሰዎች በተጨባጭ እየቀረቡ አይደለም በሚል ምክንያት የአመልካቾችን የዋስትና መብት በመንፈግ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1.በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የምዕራብ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 61944 ሐምሌ 25 ቀን 2014 ዓ.ም የአመልካቾችን የዋስትና መብት በመንፈግ የሰጠው ብይን፤ ይህን ብይን በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 401575 ነሐሴ 13 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 406112 ነሐሴ 20 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2.ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገጸለው ምክንያት አመልካቾች በዋስ ሆነው ጉዳያቸውን ሊከታተሉ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
3.አመልካቾች እያንዳንዳቸው ለብር 20000  / ሀያ  ሺህ / የሚበቃ ዋስ ሲያቀርቡ ወይም ገንዘቡን ሲያስይዙ በሌላ ጉዳይ የማይፈለጉ መሆኑ ተረጋግጦ  በዋስ ሆነው ጉዳያቸውን እንዲከታተሉ ተወስኗል፡፡

ትዕዛዝ

- የምዕራብ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከላይ የተመለከተውን የዋስትና መጠን በማስጠራት አመልካቾችን ከእሥር እንዲለቃቸው ታዟል፡፡ በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽም የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ይድረሰው፡፡
- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት
አ/ኃ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ